# ***በኪቺነር፣ ዋተርሉና ጉዌልፍ የሚገኙ ኢትዮጵያዊያን እና ትውልደ ኢትዮጵያዊያን 6ኛውን የታላቁ ህዳሴ ግድብ የመሰረት ድንጋይ የተቀመጠበት ቀን በዓል አከበሩ፣***





ከበዓል ዝግጅቱ ተሳታፊዎች በከፊል፣

ቅዳሜ ግንቦት 26 ቀን 2009 ዓ.ም በኪችነር፣ ዋተርሉና ጉዋልፍ ነዋሪ የሆኑ ኢትዮጵያዊያን እና ትውልደ ኢትዮጵያዊያን የታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ግንባታ የመሰረት ድንጋይ የተቀመጠበትን 6ኛ ዓመት በዓል በማክበር ለግድቡ ግንባታ የሚውል የገቢ ማሰባሰቢያ ፕሮግራም አካሂደዋል፡፡ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ግንባታ የመሰረት ድንጋይ የተቀመጠበትን 6ኛ ዓመት ምክንያት በማድረግ የተዘጋጀው የገቢ ማሰባሰቢያ መድረክ በኪችነር፣ ዋተርሉና ጉዋልፍ የኢትዮጵያ ህዳሴ ም/ቤት ከኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ኤምባሲ (ኦታዋ) ጋር በመተባበር የተዘጋጀ ሲሆን በገቢ ማሰባሰቢያ ፕሮግራሙ ላይ 100 የሚሆኑ በኪችነር፣ ዋተርሉና ጉዋልፍ እንዲሁም አካባቢው የሚኖሩ ኢትዮጵዊያንና ትውልደ ኢትዮጵያዊያን በተገኙበት ዝግጅቱን በደመቀ እና በተሳካ ሁኔታ ለማካሄድ ተችሏል፡፡



*የኪችነር፣ ዋተርሉና ጉዌልፍ ህዳሴ ም/ቤት አመራሮች በጋራ*

*ስለበዓሉ መግለጫ ሲሰጡ፣*

ከህዳሴ ም/ቤቱ አመራሮች መካከል አቶ ተስፋ ለአከማርያም፣ ወ/ሮ ማማየ ይመኙህል እና አቶ ኤልያስ አዋሌ በጋራ ባደረጉት ንግግር በቅድሚያ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ግንባታ የመሰረት ድንጋይ የተቀመጠበትን 6ኛ ዓመት ምክንያት በማድረግ በተዘጋጀው የገቢ ማሰባሰቢያ መድረክ ላይ ለመገኘት እንኳን ደህና መጣችሁ በማለት በዝግጅቱ ላይ ለተገኙ ተሳታፊዎች በራሳቸው እና በህዳሴ ም/ቤቱ ስም የተሰማቸውን ደስታ እና ምስጋና አቅርበዋል፡፡ በመቀጠልም ለታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ግንባታ የፋይናንስ ድጋፍ በማድረግ የግድቡ ግንባታ እንዲፋጠን በኪችነር፣ ዋተርሉና ጉዌልፍ እንዲሁም አካባቢው የምንገኝ ኢትዮጵዊያንና ትውልደ ኢትዮጵያዊያን አቅማቸው በፈቀደው ሁሉ የበኩላቸውን ድጋፍና ትብብር በማድረግ ላይ እንደሚገኙ እና ይህን የጀመሩትንን ድጋፍና ትብብርም የግድቡ ግንባታ ተጠናቆ ለታሰበው አላማ እስኪውል ድረስ አጠናክረው የሚቀጥሉ መሆኑን ገልጸዋል፡፡




*አቶ ፈለቀ መኮንን፣ በኦታዋ የኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ኤምባሲ የዳያስፖራ ተሳትፎ ዘርፍ ኃላፊ*

*ለበዓሉ ታዳሚዎች ንግግር ሲያደርጉ*

አቶ ፈለቀ መኮንን፣ በኦታዋ የኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ኤምባሲ የዳያስፖራ ተሳትፎ ዘርፍ ኃላፊ ታዳሚውን የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ግንባታ የመሰረት ድንጋይ የተቀመጠበትን 6ኛ ዓመት ምክንያት በማድረግ በተዘጋጀው የገቢ ማሰባሰቢያ መድረክ ላይ ለመገኘት እንኳን ደህና መጣችሁ ካሉ በኋላ  እለቱን አስመልክቶ ከክብርት አምባሳደር ብርቱካን አያኖ፣ በካናዳ የኢፌዴሪ ልዩ መልዕክተኛ እና ባለሙሉ ስልጣን አምባሳደር የተላከውን መልዕክት ለዝግጅቱ ተሳታፊዎች አቅርበዋል፡፡ ክብርት አምባሳደር ብርቱካን አያኖ በላኩት መልዕክት ታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ የመሰረት ድንጋይ ከተጣለበት ከመጋቢት 24 ቀን 2003 ዓ.ም ጀምሮ በኪችነር፣ ዋተርሉና ጉዋልፍ እንዲሁም አካባቢው የምትኖሩ ኢትዮጵያዊያንና ትውልደ ኢትዮጵያዊያን አቅማችሁ በፈቀደው ሁሉ  በተለያዩ መንገዶች ለታላቁ ህዳሴ ግድብ ግንባታ ከፍተኛ ትብብርና ድጋፍ እያደረጉ እንደሚገኙ፣ "ታላቁ የህዳሴ ግድባችን የሀገራችን ህብረዜማ፣ የህዳሴአችን ማማ" በሚል መሪ ቃል የሚከበረው የዘንድሮው 6ኛው ዓመት በዓል አከባበር የግድቡ ግንባታ እመርታ አሳይቶ በተለይም ከ16ቱ የሀይል

ማመንጫ ተርባይኖች መካከል 2ቱ በድምሩ 700 ሜጋ ዋት በላይ በሚያመነጭበት ወቅት የሚከበር በመሆኑ ሁሉም ህዝባችን የላቡን አሻራ ያሳረፈበት ግድብ ፍሬ ተቋዳሽ መሆኑን እና "**የይቻላል**" መፈክራችንን ትክክለኛነት የምናበስርበት በመሆኑ ልዩ እንደሚያደርገው ገልጸው፣ የህዳሴ ግድባችን የኤሌክትሪክ ኃይል ከማመንጨት በተጨማሪ የጣና ሐይቅን ሶስት እጥፍ ሐይቅ በመፍጠር ለዓሳ እርባታና ለቱሪዝም መስህብነት፣ የግድቡን ሐይቅ ተከትሎ የሚፈጠረው ደን የአየር ንብረት ለውጥን ለመከላከል፣ ለጎረቤት ሀገሮች ኤሌክትሪክ በመሸጥ የውጭ ምንዛሪ ማስገኘትና አካባቢያዊ ትብብር የማጠናከር፣ ወዘተ ጥቅሞች እንዳሉትና በዋናነት ግን የ"**ይቻላል**" መንፈስን በህዝባችን ውስጥ የሚያሰርጽ የባንዲራ ፕሮጄክታችን እንደሆነ ገልጸዋል፡፡ በመጨረሻም የህዳሴ ግድባችንና ሌሎች ዘርፈ ብዙ የልማት ውጥኖቻችንን እጅ ለእጅ ተያይዘን በጽናት ከዳር ለማድረስ በድጋሚ ኃይላችንን አስተባብረን እንድንነሳ በዚህ አጋጣሚ ጥሪዬን አቀርባለሁ ካሉ በኋላ፣ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ግንባታ የመሰረት ድንጋይ የተቀመጠበትን 6ኛ ዓመት ምክንያት በማድረግ የተዘጋጀው ይህ መድረክ የተሳካ እንዲሆን ከፍተኛ ጥረት ላደረጉት ለኪችነር፣ ዋተርሉና ጉዋልፍ የኢትዮጵያ ህዳሴ ም/ቤት አመራርና አባላት እንዲሁም በተለያየ መንገድ ድጋፍ ላደረጉ ወገኖች ሁሉ ከፍ ያለ ምስጋና በማቅረብ ንግግራቸውን አጠቃለዋል፡፡



*ዕለቱን ለመዘከር የተዘጋጀው ኬክ ሲቆረስ፣*





***በእለቱ የዝግጅቱ ተሳታፊዎች በኢትዮጵያ ብሔር ብሔረሰቦች ሙዚቃ ሲዝናኑ፣***

በዚህ የገቢ ማሰባሰቢያ ዝግጅት ላይ በአካባቢው ከሚኖሩ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን በተጨማሪ የካናዳ ዜጎች የተገኙ ሲሆን፣ በአገራችን ብሔር ብሔረሰቦች ሙዚቃ ሲዝናኑ አምሽተዋል፡፡

መስከረም 29 ቀን 2009 ዓ.ም

የኢፌዲሪ ኤምባሲ

<u>ኦታዋ</u>